አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ-የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ/ም

በአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ
አስተዳደር ጠባቂነት የወጣ

**1st year NO. 5**
**ADDIS ABABA 27th Feb. 2003**


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፺፭
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍርድ ቤቶች
የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ……ገጽ ፴፱


CONTENTS


Proclamation No. 4/2003
Addis Ababa City Judicial Administration
Commission proclamation ------------ Page 39


## የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች

## የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የከተማው የዳኝነት አካል ሆነው በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ የተቋቋሙ በመሆኑ ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድን በበላይነት የሚመራ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በማቋቋም የዳኝነት ነፃነትን በማረጋገጥ የዳኝነት አስተዳደርን ከማናቸውም አካል ወይም ባለስልጣን ተጽእኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም አንቀጽ ፵፬(፩) እና ፷፮(፪) በተደነገገው መሠረት የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## *ADDIS ABABA CITY*

## *JUDICIAL ADMINSTRATION COMMISSION*

## *PROCLAMTION No. 4/2003*

WHEREAS, the Addis Ababa city courts are established as part of judicial bodies of the City in accordance with Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 311/2003;

WHEREAS, It is found necessary to establish a Judicial Administration Commission in the Addis Ababa City Courts which directs judicial administration in ensuring judicial independence so as to independently administer the judicial free from the interference of any organ or official;

NOW, THEREFORE, in accordance with Articles 44/1/ and 66/2/ of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation NO. 311/2003, the provisional government of the city proclaims as follows.

### 1. *Short Title*

This proclamation may be cited as the "Addis Ababa City Courts Judicial Administration Commission Establishment proclamation No. 4/2003."


አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ 2445
Addis Negari Gazeta P.Box 2445



ያንዱ ዋጋ…
Unit price…17.50

፪ <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩. “የዲሲፕሊን ጥፋት” ማለት በፍርድ ቤቱ የዲሲፕሊንና የሥነ ምግባር ደንብ የተመለከተው ጥፋት ነው፤

፪.“ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ” ማለት በዲሲፕሊንና በሥነ ምግባር ደንብ የተመለከተውን መተላለፍ፣ ተፈላጊ የጥራትና የብዛት መለኪያ ያላሟላ ሆኖ የዳኝነት ሥራው ላይ ሙያው ከሚጠይቀው የትምህርትና የልምድ ችሎታ በታች በሆነ የሕግና የፍሬ ነገር ስህተት የሚፈጽምን ወይም ከሚገባው ጊዜ በላይ ጉዳዮች የሚያጓትትን ይጨምራል፤

፫.“ዳኛ” ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ተሹሞ የሚሠራ የፍርድ ባለስልጣን ነው፡፡

፪. <u>የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከዚህ በኃላ “ጉባዔ” እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፫. <u>የጉባዔው አባላት</u>

፩. ጉባዔው የሚከተሉት አባለት ይኖሩታል፤

ሀ ) የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ………………. ሰብሳቢ፣

ለ) የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ምክትል ኘሬዲዳንት ……………..አባል፣

ሐ) በከተማው ምክር ቤት የሚወክሉ ሁለት አባላት …………………………. አባላት፣

መ) የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ………………………… አባል፣

ሠ) በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚወከል አንድ ሰው ……………………… አባል፣ እና

ረ) በከተማው ፍርድ ቤት ዳኞች የሚመረጥ አንድ ዳኛ ………………….. አባል፡፡

፪. ጉባዔው የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል፡፡

፫. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ምክትል ኘሬዚዳንት ሰብሰባውን ተክቶ ይሠራል፡፡

፬. <u>የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር</u>

ጉባዔው ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. ለዳኝነት ብቁ የሆኑ ዳኞችን በመምረጥ በከተማው ምክር ቤት እንዲሾሙ በፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከሚሰጠው አስተያየት ጋር የራሱን አስተያየት በማከል ለከንቲባው ያቀርባል፣

፪. የከተማውን ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

፫. የፍርድ ቤቱን ዳኞች የሥነ ምግባርና የዲሲፕሊን ደንብ ያፀድቃል፤

፬. ስለዳኞች ዝውውር፣ ደመወዝ፣ አበል፣ ዕድገትና ምደባ በመንግሥት ፓሊሲ መሠረት ይወስናል፤ ስለዳኞች የሕክምናና ሌሎች ማበረታቻዎች አፈፃፀም በማጥናት ለከንቲባው ያቀርባል፤

፭. ስለዳኞች ስንብትና የዲሲኘሊን ጥፋት የሚቀርቡለትን ጉዳዮች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳኛ ከሥራ ታግዶ እንዲቆይ ለማድረግ ይችላል ፡፡ ዝርዝሩ በጉባዔው በሚወጣ የዲሲኘሊን አፈፃፀም የሥነ ሥርዓት መመሪያ ይወስናል፡፡

2. *Definitions*

In this proclamation:

1) “ Disciplinary offence” means the offence indicated in the disciplinary and ethics regulations of the Court;

2) “Gross incompetence and inefficiency” means failure to fulfill the quality and quantity standards of the discipline and ethics regulations and it includes one who commits error of law or fact not attributable to the training and experience that the judicial profession requires and one that delays cases beyond a reasonable time;

3) “Judge” means an official of the court appointed to give decisions in the Addis Ababa City Courts.

2. *Establishment of the Judicial Administration Commission*

The Judicial Administration commission of the Addis Ababa City Courts which is called “Commission” from now on wards shall be established by this proclamation

3. *Members of the Commission*

1) The Commission *shall* have the following members:

(a) President of the City Appellate Court ----------- Chairperson;

(b) Vice President of the City Appellate Court----- member;

(c) Two persons designated by the City Council--- member;

(d) President of the City First Instance Court------- member ;

(e) One person designed by Federal Courts--------- members;’

(f) One judge elected by judges of the City Courts- member;

2) The Commission shall have a Secretary.

3) The vice president of the Appellate Court shall act on behalf of the President in the absence of the latter.

4. *Power and Functions of the Commission*

The Commission shall have the following powers and functions to:

1) Select and present to the Mayor eligible judges for their appointment by the city council after soliciting the opinion of the Federal Judicial Administration Commission and in complementing its own opinion.

2) Direct and follow-up judicial operation in the City Courts;

3) Approve the ethics and disciplinary regulation of the judges of the courts;

4) Determine, in accordance with Government policy the transfer, salary, allowance, promotion and placement of judges; study and make proposals to the mayor on the implementation of medical and other benefits/incentives;

5) Investigate and decide on cases submitted to it regarding termination of appointment and cases of disciplinary offences of judges, where it finds it necessary it may suspend the judge from office pending its decision and the details thereof shall be defined by the disciplinary procedures of the commission.

፭. ስለጉባዔው ስብሰባ

፩. ጉባዔው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
፪. ከጉባዔው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል ፡፡
፫. የጉባዔው ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
፬. የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም የጉባዔ አባል የሆነ ዳኛ ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ዳኛው በጉባዔው ስብሰባ በአባልነት መቀመጥ አይችልም፡፡
፭. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔው የራሱን የስብሰባ መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፡፡

፮. የጉባዔው ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

የጉባዔው ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የጉባዔው ጽሕፈት ቤት በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
፪. የጉባዔው ስብሰባ ይጠራል፤
፫. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤
፬. የዕጩ ዳኞችን አጭር የትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ መግለጫ በማዘጋጀት ለጉባዔው ያቀርባል፣ በጉባዔው የተመረጡትን ዕጩ ዳኞች ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

፯. በዳኝነት ለመመረጥ የሚያበቁ ሁኔታዎች

፩ በከተማው ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ለመሾም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፤

ሀ) ለፌዴራል ሕገመንግሥቱና ለከተማው ቻርተር ታማኝ የሆነ፣
ለ) በሕግ ትምህርት የሰለጠነ እና በቂ ተግባራዊ ልምምድ ያለው፣
ሐ) በታታሪነቱ፣ በፍትሐዊነቱና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፣
መ) በዳኝነት ሥራ ለመሰማራት ፈቃደኛ የሆነ፣ እና
ሠ) ዕድሜ ከ ፳፭ ዓመት ያላነሰ ፡፡

፪. ማንኛውም ሰው በመንግሥት ሕግ አውጪ ወይም ሕግ አስፈፃሚ ውስጥ ወይም በማንኛውም የፓለቲካ ድርጅት በአባልነት በሚያገለግልበት ጊዜ አጣምሮ የዳኝነት ሥራ ሊሰራ አይችልም፡፡

፰. ስለዳኞች ከሥራ መሰናበት

፩ የከተማው ፍርድ ቤቶች ዳኛ ከሥራ የሚሰናበተው

ሀ) ሥራውን ለመልቀቅ ሲፈልግ የሁለት ወር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤
ለ) በሕመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ተብሎ ሲወሰን፤
ሐ) ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ተብሎ ሲወሰን፤
መ) የዳኞች የዲሲፕሊንና የሥነ ምግባር ደንብ ተላልፎ የደዲፕሊን ጥፋት በመፈፀም ከሥራ እንዲሰናበት ሲወሰን፤ ወይም
ሠ) የጡረታ ዕድሜ ሲደርስ፤ ይሆናል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) (ሐ) እና (መ) በተገለጹት ምክንያቶች የሚሰጥ የዳኛ ከሥራ መሰናበት ውሣኔ በከተማው ምክር ቤት ከግማሽ በላይ በሆነ ድምጽ መጽደቅ አለበት፡፡

*5. Meetings of the commission*

1) The Commission shall have a regular meeting once in every month. Extraordinary meetings may be called where necessary.
2) There shall be a quorum where more than half of the members of the Commission are present in the meeting.
3) A decision in the Commission shall be passed by majority vote. The Chairperson shall have a costing vote in case where there is a tie.
4) Any judge whose disciplinary case is under the consideration of the Commission may not attend the meeting at the time of deliberation as a member.
5) Without prejudice to the provisions of this Article, the Commission may issue its own internal regulations.

*6. Power and Functions of the Chairperson of the Commission*

The Chairperson of the Commission shall have the following powers and functions to፡

1) Direct and supervise the secretariat of the commission ;
2) Call the meetings of the commission;
3) Chair the meetings of the commission;
4) Prepare summary of the curriculum vitae of candidate judges for consideration of the commission; forward the list of candidate judges selected by the commission to the concerned bodies.

7. *Eligibility for judicial appointment*

1) The following requirements shall be fulfilled for judicial appointment in the city courts:
(a) Loyalty to the federal constitution and the city charter;
(b) Legal training and warranted practical experience;
(c) Commendable for diligence, sense of justice and ethics;
(d) Voluntary to serve in the judiciary; and
(e) not less than twenty- five years of age.
2. No simultaneous post in the judiciary may be occupied while working as a member of the legislative, executive or any political organization.

8. *Termination of Judicial Tenure*

1) The judicial tenure of a judge in the city courts may be terminated
(a) by resignation in giving a written notice of two months;
(b) where no longer he can carry out his respond sibilates on account of illness.
(c) where gross incompetence and inefficiency has been found to be committed by a judge;
(d) where it is decided for the termination of the appointment for violation of the disciplinary and etics regulations;
(e) upon retirement

2) The decision on the termination of judicial tenure on the grounds mentioned under sub-article 1(b), (c) and(d) of this article shall be approved by simple majority vote of the city council.

፱. <u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በጉባዔው የሚታይ አቤቱታ በዳኛ ላይ ለማቅረብ ይችላል ፡፡ ዝርዝር ሥነ ሥርዓቱ በጉባዔው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፲. <u>ስለ ቃለመሐላ</u>

ዳኞች ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት የሚከተለውን መሐላ ይፈጽማሉ፡፡

"እኔ …………………… በዛሬው ዕለት የከተማው ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ተሹሜ ሥራዬን ስጀምር በከተማው አስተዳደር ምክር ቤት የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት በታማኝነትና በቅንነት ለመፈፀም ቃል እገባለሁ፡፡"

፲፩ <u>ደንብና መመሪያዎች ስለማውጣት</u>

፩. የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ማውጣት ይችላል፡፡

፪. ጉባዔው ለዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ማውጣት ይችላል፡፡

፲፪. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣
የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም.

የአዲስ አበባ ከተማ
ጊዜያዊ አስተዳደር

9. *Petition*

Any person may lodge a petition against a judge on matters to be considered by the commission in accordance with this proclamation. The details of procedures shall be defined by directives of the commission.

*10. Oath*

Judges shall declare on oath before commencing their responsibilities as follows;
"I…… when on this date commence my responsibility as a judge of the city court pledge to carry out faithfully and with integrity the high responsibility entrusted to me by the council of the city Government."

*11. Power to issue regulations and directives*

1) The Cabinet of the City Government may issue regulations necessary for the implementation of this proclamation.
2) The Commission may issue directives necessary for the implementation of this proclamation and regulations issued under it.

*12. Effective Date*

This proclamation shall come in to force as of the 27th day of February, 2003

*Done at Addis Ababa*
*This date of 27th of February 2003.*

*Provisional Government of Addis Ababa City*